# ምን ብለው ይመሰክሩ?

ገዳማትና ዋሻዎች፤ ደብርና ደጀ-ሰላሙ፣
መነኩሴ ቆብ ጥሎ ሲሄድ፤ አቡን ሲቀጥፍ እያዩ፣
ስለ እምነት ቢጠይቋቸው፤ ምን ብለው ይመሰክሩ?

የአላህ ማምለኪያ መስጊዶች፤ ቅዱሱ መጻፍ ቁራኑ፣
ሼሁ ገዳይ ሲያሞካሽ፤ ሚችን ሲወቅስ ሲያዩ፣
ዳኛው ተበዳይ ኮንኖ፤ ወህኒ መዶሎን ሲሰሙ፣
ዛሬ ቢጠይቋቸው፤ ስለአቢሲኒያ ምን ይሉ?

ነጭ ጢምና ጭራ፤ እንዲሁም በራ ሽበቱ፣
ሽምጋይ በእርቅ ሲያደላ፤ ለበዳይ ሲፈርድ ያዩቱ፣
አጥብቀው ቢጠይቋቸው፤ ስለ እርቅ ፍትህ ምን ይሉ?

ቆመው የሚያስተውሉት፤ ገደል ተራራዎቹ፣
እነ ራስ-ዳሽን ጭላሎ፤ በደኖ የረር ከረዩ፣
እርስ በእርስ ስንጨፋጨፍ፤ ስንገዳደል ያዩቱ፣
በከንቱ ስለጠፋው ነፍስ፤ ቢጠይቋቸው ምን ይሉ?

ሐይቁ ጅረቱ ኩሬው፤ ታላላቆቹ ወንዞቹ፣
እነ አባይ አዋሽ ተከዜ፤ ባሮ ሸበሌ ሌሎቹ፣
የድሃ ልጅን ፈርስ ጎራሾች፤ ደሙንም ጠራጊዎቹ፣
በግፍ ስላለቀው ሕዝብ፤ ምን ብለው ይመሰክሩ?

ግራር ሰንሰሉ ግራዋው፤ ሎጋው ባህር ዛፍ ችፍርጉ፣
አድባሩ ቅዬው ሰፈሩ፤ መንደር መንገዱ ቀበሌው፣

ሰው ታስሮ አሳር ሲበላ፤ ተገድሎ ሲጣል ያዩቱ፣
አንደበታቸው ተከፍቶ፤ ምስጢሩን ሁሉ ቢያወጡ፣
ለአለም ምን ያሳውቁ፤ ምን ብለው ይመሰክሩ?

የሰው ማጎሪያ በረቶች፤ ጥቅጥቅ ጨለማ ቤቶቹ፣
ማእከላዊ ቃሊቲ፤ ዝዋይ ሰንዳፋ ሮቢቱ፣
ሰው በእሳት ሲጠበስ፤ በቁም ሲገፈፍ ያዩቱ፣
በብሶት በጭንቅ ታፍነው፤ ትናጋቸውን ቢከፍቱ፣
እንዴት ብለው ይጮሁ፤ ምን አይነት ቃልስ ይሰጡ?

ንጹሐን በባሩድ ሲፈጁ፤ አፏን ቦግ አርጋ ዋጪቱ፣
የልጅ አስከሬን ሰልቅጣ፤ የእናትን እንባ ጠጪቱ፣
ንስሃ ግቢ ብትባል፤ ምንድን ትናዘዝ ምድሪቱ?

ገዳም አድባራት መስጊዶች፤ ደጀ-ሰላሙ ታቦቱ፣
ባህርዛፍ ግራር ሰንሰሉ፤ ውልክፋ ግራር ችፍርጉ፣
የግፍ ማምረቻው ፍርድ ቤት፤ የዜጎች በረት ከርቸሌው፣
አድባሩ ቅዬው ሰፈሩ፤ መንደር መንገዱ ቀበሌው፣
ወንዞች ጅረቶች ተራሮች፤ ከላይ እስከ ታች ምድሪቱ፣
እምነት ህሊናን ደፍጥጠን፤ አብደን ስንሮጥ ያጤኑ፣
እርስ በእርስ ስንጨፋጨፍ፤ ስንጨካከን ያዩቱ፣
ቢጠይቋቸው ምን ይሉ፤ ምን ብለው ይመሰክሩ?

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥር ሁለት ሺ ሶስት ዓ.ም.